**ማስጠንቀቅያ/ ከቤት ያለመውጣት ትእዛዝ**

**እውነታዎች**: ባለስልጣኖች፡ በሲያትል ውስጥ ለሚገኙ ኣንዳንድ ኣካባቢዎች ሰው ከቤት እንዳይወጣ የሚያዝ ትእዛዝ ኣውጥተዋል። ይህም ማለት በወቅቱ ያጋጠመው ኣደጋ፡ ውጭ ከመውጣት ይልቅ ቤት ውስጥ መቆየት ራስን ከኣደጋ ለመከላከል የተሻለ መሆኑን ያመለክታል ማለት ነው። የኣደጋውን ትክክለኛ ሁኔታ ኣስቀድሞ ለማውቅ የሚያስችል መረጃ ቀደም ሲል ወይም በፍጥነት ስለማይገኝ ቤት ውስጥ መቆየት የተሻለ ይሆናል።

**ምን ማድረግ ያስፈልጋል:**

- ቤት ውስጥ ለመቆየት መዘጋጀት፡ ቤተሰቦችዎንና ከእርስዎ ስር ያሉ ለማዳ እንስሳዎችዎን ቤት ውስጥ ማስገባት፡ በሮችን፡ መስኮቶችን እንዲሁም የእሳት ማንደጃ በሮችን ይዝጉ፡ ይቆልፉም፡ በየደጃፉና በማናቸውም ንፋስ ሊያስገቡ በሚችሉ በሮች ስር እርጥብ ፎጣዎችን ያኑሩ።
- ማናቸውንም ማቀዝቀዣም ሆነ ማሞቅያ ማጥፋት።
- በእርስዎና በውጭ ባለው ኣየር መካከል ማናቸውም ግንኙነት ወይም ክፍተት እንዳይኖር፡ የውጭ ኣየር ሊያስገቡ የሚችሉ ቀዳዳዎችን በእጅ ባሎት ማፈኛ ለመዝጋት ተዘጋጁ።
- ባለስልጣኖች" ኣሁን ውጭ ለመውጣት ይቻላል" የሚል መረጃ እስኪሰጡ ድረስ፡ ካሉበት የመጠለያ ቦታ ወይም ቢትዎ ወይም ህንጻ ኣለመውጣት።
- ኣደጋውን በሚመለከት ኣዲስ መረጃ እንዳለ ለማወቅ በቀጣይነት ሬድዮ ተከታተሉ ።
- ***ይህንን መልእክት ለመረዳት፡ ለማየትም ሆነ ለመስማት የማይችል የሚያውቁት ሰው ካለ፡ እባክዎትን መልእክትቱ ኣስረድዋቸው።***

**ጠቃሚ ዌብሳይቶች:**

http://www.kingcounty.gov/safety/prepare/residents-business/PersonalPreparedness/ShelterInPlace.aspx

http://www.ready.gov/shelter

http://emergency.cdc.gov/preparedness/shelter/